ኢየሱስ የሚለዉ፤ ያለውና የነበረው የሚመጣውም ሁሉን የሚገዛ ጌታ እምላክ፤ አልፋና ዖሜጋ እኔ ነኝ ይላል... እንዲህም አለኝ አትፍራ ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ ሞቼም ነበርሁ (ሞትን ለዘላለም ለመዋጥ ኢሳ 25:-8) እነሆም ከዘላለም (ዘመን ከማይቆጠርለት) እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ነኝ የሞትና የሲኦልም መክፈቻ አለኝ በማለት የሞትን ከንቱነት ለማሳየትና ሞትንም ለዘላለም ለመዋጥ እንጂ ዘላለማዊ ሕያውነቱ እንዳልተነካ ያረጋግጣል:: ራእይ 1:-8 ቁ 17-18:: ሚክ 5:-2-4:: 1ኛዮሐ 1:-3:: ዮሐ1:-1-14:: ኤር 23:-5-6:: ራእይ 5:-13

ሰዉ የሚለዉ:- መላዕክት ስግደት ሊቀበሉ ይገባል የሞቱ ጻድቃንም ሆኑ ሕያዋን መላዕክት በእነርሱ ስም ብንጸልይ ያማልዱሉ ነዉ::

ኢየሱስና መላዕክት የሚሉት ግን:- «ሰዎች ያለ መሐላ ካህናት ሆነዋልና ክርስቶስ ግን:- ጌታ አንተ እንደመልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘላለም ካህን ነህ ብሎ ማለ አይጸጸትም ብሎ ቡተናገረለት ከመሐላ ጋር ካህን ሆኖአልና ያለ መሐላ ካህን እንዳልሆነ መጠን እንዲሁ ኢየሱስ ለሚሻል ኪዳን ዋስ ሆኖአል እነርሱም እንዳይኖሩ ሞት ስለ ከለከላቸው ካህናት የሆኑት ብዙ ናቸው እርሱ ግን ለዘላለም የሚኖር ስለ ሆነ የማይለወጥ ክህነት አለዉ፤ ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል»። ለእነርሱም አማላጅ ስለሚያስፈልጋቸዉ ሊያማልዱ አይበቁም ዕብ 7:-20-28 መላዕክትም እግዚአብሔር ቀናተኛና ክብሩን ለማንም የማያካፍል መሆኑን አውቀውና ፈርተው ለእኛ እንዳትሰግዱ ተጠንቀቁ ብለው በራእይ 19:-9-10:: 22:6-9:: ኢሳ 42:-8:: አስረድተዋል።

ሰዉ የሚለዉ:- 318 ሊቃውንት በኒቂያ የወሰኑት ቃለ ጉባኤም እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ይታመንበታልና መመሪያችን ነው የሚል ሲሆን::

ኢየሱስ የሚለዉ፤ በቃሌ ላይ የሚጨምር ወይም ነጥብም እንኳ የሚቀንስ መቅሰፍት ይጨመርበታል ነው:: ማቴ 5:16-20:: ገላ 1:-6-12:: ራዕይ 22:18-20:: ማር 8:-38:: 2ኛቆሮ 11:-1-4:: 2ኛጴጥ 3:-16-18::

ሰዉ የሚለዉ:- በእግዚአብሔር ግራና ቀኝ የተቀመጡ እግዚአብሔር ወልድ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አሉ የሚል ነው::

ኢየሱስ የሚለዉ፤ «እነሆም ዙፋን በሰማይ ቆሞአል በዙፋኑም ላይ ተቀማጭ ነበረ በማለት በሰማይ አንድ ዙፋንና አንድ ተቀማጭ ብቻ እንዳለ ነው ራእ 4:-2 «በረከትና ክብር ምስጋም ኃይልም ከዘላለም እስከ ዘላለም በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ለበጉም ይሁን» በማለት በአንዱ ዙፋን ላይ የተቀመጠው አብ የተዋሐደው ኢየሱስ ብቻ እንደሆነ ያረጋግጣል በአንድ ዙፋን ሦስት ነገሥታት አይቀመጡምና:: ከእርሱ በፊት አምላክ የለም ከእርሱ በኋላም አይሆንም:: ኢሳ 43:-10-12:: 44:-6-8:: 44:-24::

ሰዉ የሚለዉ:- የተወለደውም የሞተውም እግዚአብሔር ነዉ የሚል ሲሆን



ኢየሱስ በቃሉ የሚለዉ ግን :- ወላጅ አባቱ አብ፣ የተወለደው ሰው የሆነው ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ነው 1ኛጢሞ 2:-5-7:: «ብእኔ እንደምታዩት መንፈስ ሥጋና አጥንት የለውምና እኔን ዳሳችሁ እዩ» ብሎአቸዋልና ሉቃ 24:-39:: ኢየሱስ በሥጋ እንደመጣ የማይታመን ከእግዚአብሔር አይደለም ተብሎም ተጽፎአልና 1ኛ ዮሐ4:-1-3:: 2ኛዮሐ ቁጥር 7:: ስለዚህ ኢየሱስ በሥጋ ሲሞት በመንፈስ ግን የዘላለም አባት ነዉና ሕያዉ ነዉ 1ኛጴጥ 3፥18። ኢሳ 9፥6 ራእይ 1፥8 ቁ 17-18።

ሰዉ የሚለዉ ግን:- የአንድ አምላክ አማኞች ሦስት ሥላሴን ይከዳሉ ነዉ።

ኢየሱስ የሚለዉ፤ ብቻዉን ያለዉን ኢየሱስ ክርስቶስን ይክዳሉ ነዉ ይሁዳ 3-4። ኢሳ 44፡ 6-8 ቁ 24 ዘጸ 20፥3-5

ሰዉ የሚለዉ:- በሥላሴዎች ስም መጸለይ ይገባናል ነዉ።

ኢየሱስ የሚለዉ፤ «እስከአሁን በስሜ ምንም አለመናችሁም ደስታችሁ ፍጹም እንዲሆን ለምኑ ትቀበሉማላችሁ» ነዉ ዮሐ 16፥24። በሰማያት ያለዉ አባት አንድ ብቻ ስለሆነ አባቶቻችን ሆይ ሳይሆን አባታችን ሆይ በሉ ይላል። ስሞቻችሁ ይቀደሱ ሳይሆን ስምህ ይቀደስ በማለት ነጠላ ቁጥርን ያመለክታል በጸሎትም ጊዜ አንድነቱን እንድናዉጅ ያዛል። ማቴ 6፥9-10። ዘዳ 6፥4። ኤፌ 4፥6። ሚል 2፥10 «ለሁላችን አንድ አባት ያለን አይደለምን? አንድ አምላክስ የፈጠረን አይደለምን?» ኢሳ 9፥6።

ሰዉ የሚለዉ፤ በዘፍጥረት 18 የተጠቀሱት ሦስት ሰዎች ሥላሴዎች ናቸዉ ነዉ።

የኢየሱስ ቃል ግን፡ ሰዎቹም ከዚያ ፊታቸዉን አቀኑ ወደ ሰዶምም ሄዱ አብርሃም ግን በእግዚአብሔር ፊት ገና ቆሞ ነበር። በማለት መላዕክት እንጂ እግዚአብሔሮች እንዳልነበሩ ያረጋግጣል። ዘፍ 18፥22። 19፥1-4 ቁጥ 13። አልሸሹም ዘወር አሉ እንደሚባለዉ የዶክተር እሸቱ አባትና የመለሰ ወንዱ የተምታታ ሃሳብ የአዘሉ የስድብ መጻህፍት የአንድ አምላክ ትምህርት ለተገለጠላቸዉ ለእኛ ድጋፍ ሆነዉ በመገኘታቸዉ በገዛ ልሳናቸዉ መረታታቸዉን ያመለክታል። መጽሐፍ ቅዱስ መናፍቅ የሚለዉ ብቻዉን ያለዉን አንዱን አምላክ ሦስትም ዘጠኝም የሚሉትን ነዉ። በእግዚአብሔር ቃል የተወገዘዉ የኑቱርተሊያንን ፍልስፍና አንግቦ ከመወናበድ የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል ማመን ይሻላል። ቆላ 2፥8-10። እግዚአብሔር አብ በሥጋ ተገለጠ ስሙም አንድ አካሉም አንድ መለኮትነቱም አንድ ብቻ ነዉ። የአንድ ሰዉ ቃልና እስትንፋሱ የአካል ሦስትነት እንደማያስጡት እንዲሁ አብም መለኮትነቱ ቃሉና (ሥጋዉ) እስትንፋሱ ሦስት አካላት አያሰጡትም፤ አንድ ነዉ። ለእዉነተኛ ዳኝነት መጻሕፍቶቻቸዉንና መጻህፍቶቻችንን አንብቡና እዉነቱን ያዙ ዉሸቱን ጣሉ።

ለተጨማሪ ማብራሪያ
✉ 4442
☎ 65 34 81 አዲስ አበባ ይጠይቁ
ARTISTIC PRINTERS



http://www.sayadi-al-nas.com

# የማንን እንስማ?

## የሰውን ወይስ ክርስቶስ ኢየሱስ ያለውን እንስማ?

መጽሐፍ ቅዱስ በሙሉ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ እንጂ የሰው ቃል እንዳይደለ አረጋግጦ ማመን እጅግ አስፈላጊ ነው:: «ይህን በመጀመሪያ እወቁ! በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ፤ ሊተረጉም እልተፈቀደም ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ» 2ኛ ጴጥ 1:-20-21:: ኢሳ 34:-16

ሰዉ የሚለዉ:- የኢየሱስን ወይስ የጴጥሮስን እንስማ በማለት መጽሐፍ ቅዱስን ለሁለት አካፍሎ የሰውና የእግዚአብሔር አድርጉታል::

ኢየሱስ የሚለዉ ግን:- «የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠ ልህምና ብፁዕ ነህ እኔም እልሃለሁ አንተ ጴጥሮስ ነህ በዚህችም ዓለት ላይ ቤተክርስቲያኔን እሠራለሁ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም:: የመንግሥተሰማያትንም መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ በምድር የምታሥረው ሁሉ በሰማያት የታሠረ ይሆናል በምድርም የምትፈታው ሁሉ በሰማያት የተፈታ ይሆናል» የሚል ነው:: ማቴ 16:-17-19:: ሐዋ 2:-38

ሰዉ የሚለዉ:- አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር የኢየሱስና የመንፈስ ቅዱስ የማዳን ስም ነውና ለጥምቀት ስንጠቀምበት ያድነናል የሚል ነው::

ኢየሱስ የሚለዉ ግን:- የእግዚአብሔር አብም የወልድም የመንፈስ ቅዱስም አዳኝ ስም ኢየሱስ የተባለው ስሜ ብቻ ስለሆነ ለእግዚአብሔር አብ ክብር የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ስም ብቻ አድርጉት ነው ማቴ 1:-20-23:: ሉቃ 24:-47:: ቆላ 3:-17:: ፊል 2:-9-11:: ሐዋ 4:-12:: ዮሐ 5:-43:: 16:-23-24:: 17:-26

ሰዉ የሚለዉ:- አብና ወልድ በሰማይና በምድር ለየብቻቸው በየአካላቸው ይኖሩ ስለነበር ወልድ ወደሰማይ እያየ ይጸልያል ነው::

ኢየሱስ የሚለዉ:- «እኔና አብ አንድ ነን» እኔ በአብ አብም በእኔ ውስጥ በተዋሕዶ እንዳለን እመኑ እመኑ እመኑ ነው:: ዮሐ 10:-30:: ዮሐ14:-6-10 ኢየሱስ እርግጠኛውን የሚያስተምር የማይዋሽ መምህርና ስለራሱም ከራሱ በላይ የሚያውቅ ሌላ ስለሌለ «እውነት እውነት እልሐለሁ የምናውቀውን እንናገራለን ያየነውንም እንመሰክራለን ምስክራችንንም አትቀበሉትም ስለምድራዊ ነገር በነገርኋችሁ ጊዜ ካላመናችሁ ስለሰማያዊ ነገር ብነግራችሁ እንዴት ታምናላችሁ? ከሰማይም ከወረደው በቀር ወደሰማይ የወጣ ማንም የለም እርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው» በማለት ራሱ እንደአብ በሰማይ መሙላት እንደወልድ በምድር መኖር የሚችል እንደነበረ አረጋግጦአልና የአብንና የወልድን የአካል አንድነት ከወልድ ስለተማርን የአካል አንድነቱን ልንክድ አንችልም:: ዮሐ 3:-11-13

ሰዉ የሚለዉ:- የአንድነታቸውን ገመድ እንበጥስ ነው ንጉስ ዳዊት ሲመሰክር «አህዛብ ለምን ያጉረመርማሉ? ወገኖችስ ለምን ከንቱን ይናገራሉ? የምድር ነገሥታት ተነሡ አለቆችም በእግዚአብሔርና በመሢሁ ላይ እንዲህ ሲሉ ተማከ ማሰማርያቸውን እንበጥስ ገመዳቸውንም ከእኛ እንጣል:: በሰማይ የሚኖር እርሱ ይሥቃል ጌታም ይሣለቅባቸዋል:: በዚያን ጊዜ በቁጣው ይናገራቸዋል በመዓቱም ያውካቸዋል ይላልና:: (መዝ 2:-1-9)

ኢየሱስ የሚለዉ:- «በመጀመሪያ ቃል ነበረ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ ይህም በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ሁሉም በእርሱ ሆነ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም ቃልም ሥጋ ሆነ «እኔን ያየ አብን አይቶአል» «እኔና አብ አንድ ነን ይላል» ዮሐ 14:-7-11:: ዮሐ 1፡ 1-14። 10፡30።

ሰዉ የሚለዉ:- የኢየሱስ ስም አጋንንትን ለማስወጣትና ፈውስ ስንፈልግ የምንጠራው እንጂ ለኃጢአት ስርየት ስንጠመቅ አንፈልገውም ነው::

ኢየሱስ የሚለዉ:- በስሙ ንስሐና የኃጢአት ስርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ ለአሕዛብ (ለሰዉ ዘር) ሁሉ ማለትም ለዓለም ሁሉ ይሰበክ ነው:: ሉቃ 24:-47:: ማር 16:-15-18::ሐዋ 22:-16::ሐዋ19:-1-6

ሰዉ የሚለዉ:- በማቴዎስ ወንጌል 28:-19 የተጠቀሰው ጥምቀት የየሱስ ትዕዛዝ ስለሆነ ሐዋርያት ቢያጠምቁበትም አይለወጥም ነዉ።

ኢየሱስ የሚለዉ ግን:- ሐዋርያትን የሚሰማ እኔን ይሰማል እነርሱን የጣለ እኔን ይጥላል እኔንም የጣለ የላከኝን ይጥላል ይላል ሉቃ 10:-16 ለእናንተ የመንግሥተ ሰማያትን ምሥጢር ማወቅ ተሰጥቶአችኋል ለእነርሱ ግን አልተሰጣቸውም ማቴ 13:-11 ስለዚህ ሐዋርያት ምስጢሩ ስለገባቸው በኢየሱስ ስም ብቻ ሲያጠምቁ ኖረዋል ሐዋ ሥራ 2፡38። ሐዋ 8፡16። ሐዋ 10፡43-48። 22፡16። የማይለወጥ የዕምነት አንቀጻቸዉንም በኤፌሶን ቤተክርስቲያን ሲደነግጉ «በመጠራታችሁ በአንድ ተስፋ እንደ ተጠራችሁ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት (በኢየሱስ ስም ብቻ የሆነች) ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ ብሎአል። ኤፌሶን 4፡4-6። ሐዋ 19፡ 1-6።

ሰዉ የሚለዉ:- አንድ አምላክ በአንድ አካል በኢየሱስ ተገልጦአል የሚሉ አብንና መንፈስ ቅዱስን ከደዋል ነው::

ኢየሱስ የሚለዉ:- በወልድ የሚታመን አብ ደግሞ አለው ነው:: 1ኛዮሐ2:-23:: ዮሐ 3:-13:: ዮሐ 14:-6-10

ሰዉ የሚለዉ:- መንፈስ ቅዱስ እንደሰው አካል የሆነ አካል አለው ነው::

ኢየሱስ የሚለዉ:- መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር እስትንፋስ ስለሆነ እንደነፋስ እንደ ደመና እንደ ዘይት የሚመስል እንጂ ሥጋና አጥንት እንዳለው በሰው አካል አይመስልም ነው:: ኢዮብ 32:-8:: 33:-4:: ዘፍ 2:-7:: ሐዋ 2:-1-4:: ዮሐ 20:-22::



ሰዉ የሚለዉ:- በዘፍጥረት 1:-26 እንፍጠር ስለሚል በሰማይ ሦስት ፈጣሪዎች ነበሩ ነው::

ኢየሱስ የሚለዉ፤ በዘፍጥረት 1:-26-27 እግዚአብሔርም «አለ» በማለት፣ በነጠላ ቁጥር አንድነቱን ያመለክታል። ቁጥር 27 ደግሞ ሰውን «በመልኩ ፈጠረ» በእግዚአብሔርም መልክ «ፈጠረው» በማለት በነጠላ ቁጥር አንድነቱን አረጋገጠ በማሳየቱ አንድ እንጂ ሦስት ሆኖ አያውቅም:: በኢሳ 44:-6-8 ቁጥር 24 ደግሞ እኔ ፊተኛ ነኝ እኔም ኋለኛ ነኝ ከእኔ ሌላም አምላክ የለም እንደ እኔ ያለ ማን ነው? ... እናንተ ምስክሮቼ ናችሁ ከእኔ ሌላ አምላክ አለን? አምባ የለም ማንንም አላውቅም። ከማኅፀን የሠራህ የሚቤዥህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ሁሉን የፈጠርሁ ሰማያትን ለብቻዬ የዘረጋሁ ምድርንም ያጸናሁ እግዚአብሔር እኔ ነኝ ከእኔ ጋር ማን ነበረ? እያለ ይጠይቀናል::

ሰዉ የሚለዉ:- በዳግም ምጽአት ጊዜ አብና መንፈስ ቅዱስ በሰማይ ቀርተዉ ወልድ ብቻውን ይመለሳል ነው::

ኢየሱስ የሚለዉ፤ አምላኬ እግዚአብሔር ከቅዱሳኑ ሁሉ ጋር ይመጣል... እግዚአብሔርም በምድር ሁሉ ላይ ይነግሣል በዚያ ቀን እግዚአብሔር አንድ ስሙም አንድ ይሆናል (ዘካ 14:-1-9 ተመልከት)

ሰዉ የሚለዉ:- የአብ ልጅ እግዚአብሔር ወልድና የማርያም ልጅ ክርስቶስ በተዋሕዶ አንድ አካል ናቸው የሚል ሲሆን፤

ኢየሱስ የሚለዉ:- እኔና አብ በተዋሕዶ አንድ አካል ነን የሚል ነው ዮሐ 1:-1-14:: ዮሐ 14:6-10 አንድ ወልድ የአብ ልጅ እንጂ ሁለት ወልዶች የሉምና:: ከ325 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1050 ዓ.ም. ድረስ የነበሩትን ክርክሮች ከቤተክርስቲያን ታሪክ ተመልከት::

ሰዉ የሚለዉ:- ሚካኤል ወልድ ለመሆን ከድንግል ማርያም ተወለደ እንጂ ቃል ሥጋ አልሆነም ነው (የጆሆባ ምስክሮችን ጠይቅ)

ኢየሱስ የሚለዉ፤ ዕብ 1፡5-6 «ከመላእክትስ አንተ ልጄ ነህ እኔ ዛሬ ወልጄሃለሁ ደግሞም እኔ አባት እሆነዋለሁ እርሱም ልጅ ይሆነኛል ያለዉ ከቶ ለማን ነዉ? ደግሞም በኩርን ወደ ዓለም ሲያገባ የእግዚአብሔር መላእክት ሁሉም ለርሱ ይስገዱ ይላል «እኔና አብ አንድ ነን በእኔ የሚያምን በላከኝ ማመኑ ነው እንጂ በእኔ አይደለም እኔንም የሚያይ የላከኝን ያያል» ነዉ ዮሐ 12:-44-45:: ዮሐ 14:7-11::

ሰዉ የሚለዉ:- በሐዋርያት ሥራ 2:-38 ያለው የኢየሱስ ስም ጥምቀት ለአይሁድ ብቻ ነው አይሁድ አብንና መንፈስን ስለሚያውቁ ኢየሱስን ግን ስላልተቀበሉት ወልድን ለማስተዋወቅ የተደረገ ጥምቀት ነው የሚል ነዉ::



ኢየሱስ የሚለዉ፤ የሰው ነፍስ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ስለረከሰ ያለ ኢየሱስ ስምና ደም መታረቂያ መዳኛ የለውምና ነፍስ ሁሉ እንዲድን ከሰማይ በታች ከኢየሱስ ስም በቀር መዳኛ የለውም ነው:: ሉቃ 24:-47:: ዮሐ 14:6-7::ሐዋ 2:-38:: ሐዋ 4:-12:: ሮሜ 5:: ዮሐ1:-12:: 3:-16-18:: በአይሁድና በግሪክ ሰዉ መካከል ልዩነት የለም ተብሎ ተጽፋፎአል። ሮሜ 2፡11። 3፡20-26። ሮሜ 10፡12-13። ገላ 3፡26-28።

ሰዉ የሚለዉ:- አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በኢየሱስ ብቻ ተጠቅልሎ አንድ አካል አንድ ፈጣሪ ሆነ ስሙም ኢየሱስ ብቻ ነው የሚሉ አብንና መንፈስን ከደዋል ነው::

ኢየሱስ በቃሉ የሚለዉ ግን:- ብዙ አሳቾች ወደ ዓለም ገብተዋልና እነርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደመጣ የማያምኑ ናቸው፤ ይህ አሳቹና የክርስቶስ ተቃዋሚው ነው:: ...ለሚወጣው ሁሉ በክርስቶስ ትምህርት ለማይኖር ሰዉ አምላክ የለውም በክርስቶስ ትምህርት ለሚኖር አብና ወልድ አሉት:: ማንም ወደናንተ ቢመጣ ይህንንም ትምህርት ባያመጣ በቤታችሁ አትቀበሉት በማለት ያወግዛል 2ኛዮሐ 7-9 የክርስቶስ ትምህርት ምንድር ነው? ብለን ብንጠይቅ በዮሐ 10:-30 እኔና አብ አንድ ነን ይላል በዮሐ 14:6-11 አብና ወልድ በተዋሕዶ፣ መንፈስ በሥጋ፣ ሥጋ በመንፈስ ውስጥ በአንድ አካል እንዳሉ ያስተምራል ክርስቶስ እኔን ያየ አብን አይቶአል ብሎ ያስተምራል ሐዋርያትም የመለኮት መላት ሁሉ በሰውነት (በሥጋ) ተገልጦ ይኖራል ይላሉ:: አምላክ በሥጋ ተገለጠም ይላሉ:: አማኑኤል ሆነም ይላል ማቴ 1፡23። ኢሳ 7፡13-14። ቆላ 2:8-9:: 1ኛ ጢሞ 3:-16:: ይሁዳ ቁጥር 4 «ከብዙ ጊዜ በፊት ለዚህ ፍርድ የተጻፉ አንዳንዶች ሰዎች ሾልከው ገብተዋልና ኃጢአተኞች ሆነው የአምላካችንን ጸጋ በሴሰኝነት ይለውጣሉ:: ንጉሣችንንና ጌታችንንም ብቻውን ያለውን ኢየሱስ ክርስቶስን ይክዳሉ... ሳትሰናከሉም እንዲጠብቃችሁ በክብሩም ፊት በደስታ ነውር የሌላችሁ አድርጎ እንዲያቆማችሁ ለሚችለው ብቻውን ለሆነ አምላክና መድኃኒታችን... ኃይልም ሥልጣንም ይሁን አሜን» ይላል ቁ 24-25። ስለ ስሙም ሲናገር እኔ በአባቴ ስም መጣሁ በማለት ኢየሱስ አብ በሥጋ ሲገለጥ የተጠራበት ስም እንደሆነ ይገልጣል። ዮሐ 5፡43። ሚክ 5፡2-4። ኤር 23፡5-6። ዕብ 1፡3-4። ራእይ 3፡12። ማቴ 1፡20-23።

ሰዉ የሚለዉ፤ እግዚአብሔር አብ እግዚአብሔር ወልድ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በየአካላቸዉ አሉ ነዉ።

ኢየሱስ በቃሉ የሚለዉ ደግሞ፤ አንድ እግዚአብሔር አብና ሰዉ የሆነዉ ክርስቶስ ብቻ እንጂ ሶስት እግዚአብሔሮች የሉም ነዉ የእግዚአብሔር ልጅ በማለት ፋንታ እግዚአንሔር ልጅ እግዚአብሔር እስትንፋስ የሚል አልተጻፈምና። 1ኛጢሞ 1፡15-17። 2፡ 5-7፡3፡16። ዮሐ1፡7፡3። 1ኛዮሐ 5፡ 19-20።

ሰዉ የሚለዉ:- ኢየሱስ የዳዊት ዘር የሴት ዘር የተባለለት እንደ እኛ ሰው ስለሆነ ዘመን የሚቆጠርለት ነው የሚል ሲሆን